# ዕምባ ወደ ደም ይለወጣል !

ሐተታ ቁጥር 6

ሐምሌ 2006 ዓም

ዕምባ፤ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የመጣል። በግድና በውድ፤ በሀዘንና በደስታ፤ በስቃይና በኅመም፤ በአካል ጉዳትና በመንፈስ ስብራት፤ በአዕምሮ ድቀትና በኅሊና ሰቆቃ ምክንያት ዕምባ ይፈልቃል፤ ይፈስሣል። ከልክ በላይ ደስታ በዝቶ ሲገነፍል ደግሞ፤የሀሴት ዕምባ እያስፈነድቃል። ሀሴትና ፍስሀ ሲበዛ፤ የደስታ ሳቅ ይፍለቀለቃል ። የመከራ ኑሮ ሲደራረብ ደግሞ፤ ከልብ ስብራት፤ ከአካል ግርፋት፤ ከመንፈስ ጉዳት፤ ከተስፋ ማጣት፤ ከጥቃትና ከውርደት ብዛት የተነሳ፤ ዕምባ እንደ ጅረት ይወርዳል። ጉንጭን እያራሰ ወደ አንገት ይውርዳል። አልቃሹ እያለቀሰ፤ ሌላውን ተመልካች እያሳዘነ ያስለቅሳል። ጥቃትና ውርደት የደረሰበት ኅብረተስብ፤ በደሉን የሚወጣበት ኅይልና ጉልበት ሲያጣ፤ ቁጭቱን በዕምባ የወጠዋል። በንጉርጉሮ እራሱን እያጽናና እስከጊዜው ይቆያል ። ጥቃትና ቁጭቱን አፍኖ ይቆያል። ችግሩን በችግር እየኖረ ያሳልፋል ። ሁሉም ነገር ያልፋል። እስኪያልፍ ግን ያለፋል ! ቁጭቱን እስኪወጣ ድረስ ሰንቁን ዕምባ አድርጎ በተስፋ ኃሳብ የዘምታል ! ይመርሻል ! በእንጉርጉሮው እየተጽናና ይቆያል ! መቆየት ከተባለም ፤እስከሚቆይበት ጊዜ ይቆያል !

"መከራና ሀዘን፤ ጥቃትና ውርደት፤ በደል- ቁጭት በዝቶ፤

በመከራው ሰዓት አይዞህ የሚል ጠፍቶ፤ ረዳት አጥቶ፤

ዕምባን ማፍሰስ እንጅ ሌላ ምን ተገኝቶ፤

ኡኡታን ቢያሰሙ፤ ማን አፅናኝ መጥቶ ? "

ሰማይ-ምድሩ በተደፋበት ኅብረተሰብ ውስጥ፤ ዕምባ ሞልቶ ይተርፋል። ሰው ፍጡር በመሆኑ፤ ሲያዝን ያለቅሳል። ሲደሰት ይስቃል። ሲጠቃ እየየ ! ይላል። ሲያጠቃ ጮቤ ይረግጣል። ይፈነድቃል። ዳንኪራ ይረግጣል። በአንጻሩ ደግሞ፤ ጥቃቱን መወጣት ሲያቅተው፤ ውርደቱን መሸከም ሲሳነው፤ ይንገበግባል። ይቃጠላል። ያርራል። ይኮማተራል። ይተክናል። ሰው መሆኑንም ይንቃል። መፈጠሩን ይጠላል። ሰብዕናውን ከዕንስሳ በታች አድርጎ ይመለከታል። የተዋረደ ሰብዕናውን ለማስከበር ሲል ግን፤ ዕምባውን ወደ ደም እስከ መለውጥ ይገደዳል። ዕምባውን ወደ ደም ለመለወጥ የሚገደድበት አስገዳጅ ምክንያት፤ በዕምባ የተሞላውን የመከራ ኑሮውን ወደ ነፃነት ህይወት ለመለውጥ ሲል ነው። በሰው ልጅ የታሪክ ሂደት፤ ተበዳይ፤ በበዳይ ላይ መነሳቱና ማመጹ የነበረ ነው። ወደፊትም ይህ ሄደት ይቀጥላል። የዛሬ አስለቃሾች፤ የነገ አልቃሾች ይሆናሉ። ይኽ እንደሚሆን፤ የኅብረተስብ ለውጥ የሚያመጣው ክስተት መሆኑን ማንም ሰው ሊክድ አይችልም ።

ገፍና በድል በነገሰበት ኅብረትስብ፤ ጭቆና በተንሰራፋበት ሥርዓት፤ ፍትኅ-ርትዕ በተረገጠበት ሀገር ፤ በየትም አካባቢ ቢሄዱ፤ዕምባ የተቀላቀለበት ዋይታና ሮሮ መስማትና ማሰማት የተለመደ ነው።

ይሁንና፣ የኢትዮጵያ ዕምባ፣ እንደ ራሄል እምባ፣ ጩኸቱ የሚሰማበት ወቅት ሩቅ አይሆንም። ጭኸቱ እንዲሰማ ከተፈለገ ደግሞ፣ በዕምነት ጸንቶ፣ ተባብሮ እየታገሉ ለመሥዋዕት መዘጋጀትን ይጠይቃል። ይህ ካልሆነ ግን፣ " ዋይታና ጩኸቱ ከንቱ " ሆኖ ይቀራል። ነጻነትን ለመጎናጸፍ ከተፈለገ፣ የጥቃት ዕምባን እያደረቁ፣ የደም መሥዋዕት መክፈል ምራጭ አይኖረውም። ዘወትር በአመፀኞች የአገዛዝ ቀንበር እየተዋረዱ ከመኖር፣ ነጻነት የሚጠይቀውን የደም ዋጋ እየከፈሉ በኩራት ማለፍ የታሪክን ምዕራፍ ያስጨብጣል። እየተጠቁ የውርደት ኑሮ ከመግፋት፣ ለአንድ ቀን ጀምበር እንኳን ቢሆን ፣ ነጻንትን አይቶ መሞት ይመረጣል።

የሰው ልጅ ሲበደል፣ ሲጠቃና የመከራ ፅዋው ሞልቶ ሲገነፍልበት፣ለአመፅ ይነሳል። የአመፁ ምዕራፍ መከፈቻ እንዲሆንለትም ፣ የሚከተለው እንጉርጉሮ ያሰማል።

" ታርሶም ተሸምቶም፣ ይበላል እንጀራ፣

እንዴት አለሽ ጥቃት የሞት ባልንጀራ ! "

በመጨረሻ ለአመፅ የሚነሳው፣ ጥቃቱና ውርደቱን ለመሸከም የሚችልበት ትከሻው ሲሰበርበት ነው። ወርደቱን የሚያስተናግድበት የታጋሽነት ኀሌናው ሲሟጠጥበትና የትዕግስቱ ከረጢት ሞልቶ ሲተረተርበት፣ ትግዕስቱን ወደ አመፅ - ነበልባል ለውጦ ለአመፅ ይነሳል። ያን ጊዜ የሚያቆመውና የሚገታው ኀይል አይኖርም። የማነኛውንም ሕዝብ ትዕግስትና ቻይነት ከልኬታው በላይ ካለፈ፣ ዕምባውን ወደ ደም የሚለውጥበት ጊዜ መምጣቱ አይቀርም። የዕምባው ከረጢት ነጥፎ አንድ ዘለላ ዕምባ እንኳን ማልቀስ ይጠፋል። የደም ዕምባ ሲያለቅስ የኖረ ሕዝብ፣ ዕምባው ከነጠፈበት በኋላ የሚተርፈው ደም ብቻ ይሆናል። በዚህ ወቅት፣ ዕምባ ወደ ደም ይለወጣል ። ፍትኅ-ርትዕ በጎደልበት አገር፣ አንድ ቋጫ ዕምባ ቢያፈስሱት አዛኝና ሰሚ ስለማይኖር፣ ዜጎች ሁሉ፣ አንድ አንድ ጠብታ ደም እየከፈሉ ነጻነትን እየተጎናጸፉ ከውርደት ኖሩ መላቀቅን ሽህ ጊዜ ይመርጣሉ ። የፈልጋሉ ። ለነጻነት ሲባል ከፍተኛ ዋጋ መክፈል ደግሞ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም ሊነግረው የሚችል ያለ አይመስለንም ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ነጻነት፣ ከማንም፣ ከምንም በላይ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ኩራት ዕራቱ፣ ውርደት ሞቱ፣ ነፃነት ህይወቱ ነው።

የሀገራችን ሕዝብ ፣ ቻይነቱን ወደ ቁጣ `፣ ዕንባውን ወደ ደም የሚለውጥበት ጊዜ በቅርቡ ይመጣል ። ከዚያ በኋላ፣ " ቻይ ካመረረ ፣ በግ ከበረረ፣" እንደሚባለው፣ ወቅቱ ሲደር፣፣ የደም አቁማዳው ገንፍሎ ፣ የፈስሳል። አምባጓሮ ይቀሰቀሳል። ተበዳይ በበዳይ ላይ ይነሳል። ትዕግስት ይሟጠጣል። ተጨቋኝ በጨቋን ላይ ያምጻል። ገላጋይና ዳኛ፣ ሽምጋይና አስጣራቂ ይጠፋል። ዕምባው ደርቆበት የተነሳው ተበዳይ፣ ቆጭቱን ለመወጣት የተባበራል። ዕድሜውን በሙሉ ሲያለቅስ የኖረ ሕዝብ፣ ለነጻነቱ ሲል ደሙን ለመገበር ወደኋላ እንደማይል፣ የሰው ልጆች ታሪክ በሰፊው ጽፎታል። ሲበድለው በነበረው ግፈኛ ላይ ለማመፅ፣ ዕምባውን ወደ ደም ለውጦ ይፋረደዋል።፡ እንደ ጅረት የወረደው ዕምባው ሲደርቅበት፣ በደም አለባ ይተከዋል። በዳዮቹ ወደ ፈርድ ሸንጎ እስኪቀርቡ ድረስ፣ ደሙን ከመገበር ወደ ኋላ አይልም።

የደምን ዋጋ ለሚጠይቅ ነጻነት፣ ነጻነት ፈላጊ ዜጋ ሁሉ፣ ክፍያና አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ይጠበቅበታል። ይህንን ማድረግ ደግሞ ነጻነት የጠማው ዜጋ ሁሉ ታሪካዊ ተልዕኮ ነው። የደም ዋጋን

በሚጠይቅ ትግል፤ ሁሉም ዜጋ የሳተፍበታል እንጅ፤ መሥዋዕት የመክፈሉ ኃላፊነት ለትቂቶች ብቻ የሚተው አይደለም ። " በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ " የሚባል ምጸት አይሰራም።

" የሰው እንጀራ አውጭ እንደ ሰበጥራ፤

እኛ እየተሰዋን ሌላው በላ እንጀራ "

እየተባለ የተንጎረጎረበት የጥንት ዐርበኞችን ትካዜ፤ የሚያስታውስ ያስታውሰዋል ። በተለየም፤ የዐርበኞች ልጆች በህይውት ካላችሁ፤ ይህንን አስታውሱ! ዛሬ፤ በሀገራችን፤ የባንዳ ልጆች እያስለቀሱ፤ የዐርበኞች ልጆች የደም ዕምባ እያለቀሱ መሆናቸውን አትዘንጉ ! የተገለበጠውና የተጣመመው የሀገራችን ታሪክ ይቃናል። ዕውነተኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ተቀብሮ አይቀርም። ታሪክ ሰሪው መልዐተ ሕዝብ መሆኑ ባይካደም፤ በዚህ የቀውጢ ቀን ግን ፤ ለታሪክ ቅናዒ ይሆኑ ሰዎች/ መሪዎች የስፈልጋሉ። አንገት ደፍቶ መቋመዝ፤ ከጥቃት አያድንም ። ለነጻነት አያበቃም።

ይህንን የታሪክ ሀቅ ግን፤ በሥልጣን ላይ የተቀመጡ ሁሉ ሊያዩት፤ ሊረዱትና ሊገነዘቡት አይችሉም። የሥልጣን ጥም ዋናው በሽታ፤ ዐይነ- ኅሊናን ማሳወሩ ነው። ለዚህ ከስተት፤ በኢትዮጵያ በቅርብ የተፈራረቁት ገዥዎች እንደ ህያው ምስክርነት ይጠቅሳሉ። አምባገነኖች፤ አንድ ጊዜ እንደ ምንም ብለው ከሥልጣን ኮረቻ ላይ ከተቆናጠጡ ፤ ሬሳቸው እስኪ ወጣ ደረስ እዚያው የበሰብሳሉ እንጅ ፤ በፈቃዳቸው አይወርዱም። ወደው አይለቁም። ለሕዝብ ማስረከብ አይፈልጉም። ወትሮውኑም ቢሆን እኮ፤ አምባገነኖች ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለሕዝብ ያስረክባሉ ተብሎ አይጠበቅም! የዚህ ውጤት ደግሞ እራሳቸው ጠፍተው ሀገርንና ሕዝብን አውድመው ዘር ማንዝራታቸውን ሁሉ አጥፍተው መጥፋት ሆኗል።

ለሀገሪቱ ችግር አርቆ አስተዋይ ያልሆኑ መሪዎች፤ የኋላ ልጅ ይጨነቅበት ማለት ይቅናቸዋል ! ከኛ በኋላ ኢትዮጵያና ሕዝቧ እንደፈለጋቸው ይሁኑ ማለትን ያዘወትራሉ። እኛ ከሞትን ሰርዶ አይብቀል ባዮች ነበሩ። አሁንም ያው ነው። እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ አትኖርም በሚል ቅዠት፤ እራሳቸውን እየደለሉ ኖረው ያልፋሉ። ሀገሪቱና ሕዝቧ ግን፤ ምናልባት ለሌላ አዲስ አምባገነን ሥርዓት ይዳረጉ ይሆናል እንጅ፤ እነርሱ ግን ጠፍተው አይጠፉም። ዎያኔዎችም ጊዜያቸው ሲደርስ ያልፋሉ፡፡ ኢትዮጵያም ትኖርለች። ዎያኔዎቹ፤ ምንም ምን ቢሆን ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የደም ዕምባ እያስለቀሱ በሀገረ ኢትዮጵያ ሊኖሩ አይችሉም። አይገባቸውምም !

**"በደም የኖሩ፤ በደም ይጠፋሉ "** ነውና፤ የንጹሃንን ደም ሲያፈስሱ የኖሩ ሁሉ ደማቸው እየፈሰሰ መጥፋታቸው አይቅሬ ነው። ይህ ከስተት ደግሞ ፤ የታሪክ ሀቅ ስለሆነ መፈጸሙ አይቀርም። ይህንን መዝንጋት የተስፋ መቁረጥ ምልክት ስለሚሆን ሁሉም ዜጋ ሊጠነቀቅበትና ሊያስብበት ይገባል። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለአንዴና ለመጨረሻው ጊዜ ተባብሮ ራሱን ከጥፋት ማዳን አለበት። እራሱን እራሱ ካላዳነ ማንም ነጻ አያደርገውም ። የሕዝቡን አንድ መሆንንና የአንድነት ኅይሉም መተባበር አንገብጋቢ መሆኑን ደጋግመን የምናወሳው፤ ለጉዳዩ አስፈላጊነት አጽንዖት ለመስጠትና የመተበበሩ ጉዳይ ዕልባት ካላገኘ በተናጠል የሚደረገው መፍጨርጨር የትም እንደማያደርስ ለማሳሰብ ነው። የኅበረት ጉዳይ ተደጋግሞ የሚነሳው፤ በሦስት መሠረታዊ ምክንያቶች መሆኑን መረዳት ጠቃሚ እንደሆነ እነገነዘባለን። እናስገነዝባለንም ! እነርሱም፡-

1. ሀገራችን የብዙ ብሄር- በሄረሰብ ምደር በመሆኗ፤ ሁሉንም ያካተተ/ ኅብረተ-ሱታፌ/ ትግል ማካሄድ ለኢትዮጵያ አንድነት መሠረት ስለሚሆን ነው። በሀገሪቱ የወደፊት ዕድል ወሳኝ መሆን የሚግባው ሁሉም ዜጋ መሆን ስላለበት፤ የሁሉንም ኅሳብና ድምፅ ማካተት አስፋልጊ መሆኑ መታመን ይኖርበታል። በኅብረቱ ትግል ሂደት ሁሉም ዜጋ ከተሳተፈበት፤ ለሠላም የሚኖረው ዋስትና አስተማማኝ ይሆናል ተብሎ የታመናል።+ አንድ ባለ ነፍጥ፤ ወይም ጥቂት ለሥልጣን ያቆበቆቡ ንኡሳን ክፍሎች ብቻ በመሽቀዳደም መንግሥት ይዘናል ቢሉ ፤በሀገሪቱ ላይ ምን ያህል አደጋ እንደሚያስከትል ዎያኔንና የሎንዶኑን የ1981 ን ጉባዔ ብቻ ማጤኑ የበቃል። ያ እንዳይደገም ከተፈለገ፤ በግድ የኅብረት ትግል ማካሄድ ዋሳኝም፤ አስፈላጊም ነው።

2. የነገዋ ኢትዮጵያ ሥርዓተ- መንግሥት ደሞክራሲያዊ መስተዳደር መሆን ስለአለበት፤ የሁሉንም ፓርቲዎች ተሳትፎ ማከተት አስፈላጊ ነው። ለዚህ የፖለቲካ ሥርዓት ማረጋግጫ ሊሆን የሚችለው፤ የምድበለ- ፓርቲ ሥርዓት መኖሩ ወሳኝነቱ የሚያጠራጥር አይደለም ። የመድበለ- ፓርቲን ሥርዓት ዘር ለመትከልና ለማፍራት፤ ደግሞ የኅብረቱ ትግል መልካም ማሳ ሊሆን ይችላል። ለመሸጋገሪያ ዘመን ሂደት ምቹ ጥሪጊያም ይከፍታል። የመሸጋገሪያ ወቅት ጠቃሚና አስፈላጊ የሚሆነው፤የመረጋጋት፤ የሰላምና ዕርቅ ሁኔታን ለማንገስና ለማረጋገጥም ጭምር ይሆናል። ዕውነተኛ ሠላምና መረጋጋት፤ ዕርቅና መተማመን፤ ብሎም ተስማምቶና ተቻችሎ ሀገርን ከጥፋት አድኖ፤ ሥርዓተ-ዴሞክራሲን መገንባት የሚቻለው፤ ሁሉንም ያሳተፈ/ ያከተተ የኅብረት እንቅስቃሴ በተግባር ሲገለጽ ነው። አግላይ ፖለቲካ፤ ለኢትዮጵያ አንደነትና ልማት አይበጅም። ለሠላም ጥረትም ዕንቅፋት ነው።

3. የሀገሪቱን ፤ ውስብስብና ጥልፍልፍ፤ ሰፊና ጥልቅ፤ ዘርፈ- ብዙና አድማሰ- ግዙፍ የሆኑ ቸግሮችን ለማስወገድ የሚቻለው፤ የሀገሪቱን ዜጎች ሁሉ ያቀፈ የኅብረት ሥራ ሲከናወን ብቻ እንደሚሆን አርቆ አስተዋይ የሆነ ዘጋ ሁሉ ይስማማበታል። የተፈጥሮና ሰው-ሰራሽ ችግሮቻችንን መቋቋምና ማስወገድ የምንችለው፤ የሀገሪቱን ዜጎች፤ ከሊኅቅ- እስከ ደቂቅ ሊያሳትፍና ሊያስተባብር የሚችል ሥርዓተ- መድረክ ሲዘረጋ ነው ብለው የሚያምኑ ኢትዮጵያውያንን ቁጥር በአሃዝ መግለጽ ያዳግታል። ይህ ሀቅ ደግሞ ለነገዋ ኢትዮጵያ ብሩኅ ተስፋ ለሚመኙ ዜጎች ሁሉ ታላቅ የኅልውና ማረጋገጫ ሆኗል። በዕርግጥም፤ የሀገራችቸውን ትንሣዔ የሚመኙ ሁሉ፤ ዕምባቸውን እያበሱ ደስታቸውን የሚገልጹበት ጊዜ ዕሩቅ አይሆንም።

የኅብረት አስፈላጊነት ሦስተኛው ነጥብ የሆነውን ለማስፊር የተፈለገው፤ ከሀገሪቱ ችግሮች መፍተሄ አንጻር በማየት ነው። በተናጠል የሚሞከር የችግር አፈታት ዘዴ፤ የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች መፍታት ቀርቶ መቅረፍ እንኳን አያስችልም። መልካም ሀገራዊ ኅዳና ለመጀመር፤ መነሻው ጽኑ መሠረት እንዲሆን ያስፈልጋል። የሀገራችንን የወደፊት ፅኑ አንድነት የሚገነባው በድቡሽት ላይ አይደለም። በዘር ላይ የተመሰረተ ሥረዓተ መንግሥት፤ እንኳንስ ለ21ኛው ምዕተ ዓመት ኅብረተስብ ቀርቶ፤ ለደንጋይ-ዘመን ማኅበረ-ሰብም ቢሆን አይሰራም። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ውስጥ ያለቸው ሀገሩ ፤ በቅድመ- ቴዎድሮስ ወደነበረችበት የመሳፍንት አገዛዝ እንድትወድቅ ፍላጎት የለውም። ቋንቋንና ዘርን መሠረት ያደርገ የፖለቲካ ሥርዓትና የመንግሥት አወቃቀር፤ በነገዋ ኢትዮጵያ ቦታ አይኖረውም።

ከላይ የተጥቀሱት ሦስት ነጥቦች እንዳሉ ሆነው፤ **ለኅብረት ትግሉ መነሻና መሠረት መሆን የሚገባው ግን፤ በኢትዮጵያ ሀገራዊ / ግዛታዊ ልዕልና ፤ በዜጎቿ ዕኩልነትና አንድነት ማመን አልፋ-ዖሜጋ መሆኑን መቀበል ነው ። ይህ ጉዳይ፤ ለኅብረት ትግል ተሳታፊዎች ግዴታ ነው ።** ሀገርና ሕዝብ ከሌሉ፤ ትግልም ሆነ፤ ነጻነት፤ ዴሞክራሲም ሆነ ልማትና ብልጽግና በኅዋው ላይ ተንሳፍፈው የቅራሉ። የውሃ ሽታ ከመሆንም አያልፉ። **የአንድነት ኀይሎች ተባብረው በኅብረት ሊታገሉ የሚችሉት ደግሞ ፤ በአንድ ዓይነተኛ ጉዳይ ላይ ኀላፊነትና ግዴታ ያለባቸው መሆኑን አምነው፤ ይህንን የጋራ ኀላፊነት በጋራ ለመሸከም/ ለመቀበል ተዘጋጅተው ሲስማሙ ብቻ ነው ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነት ከሆነና፤ ዕውነት መነገር አለበትም ከተባለ፤ ዛሬ፤ ኢትዮጵያ፤ ብሄራዊ ጥቅሟን የሚያስጠብቅላትና፤ የሚከላከልላት የተደራጀ ኀይል አለ ብሎ የሚያምን የለም።** የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ ባለቤት የሌላት ሀገር ሆናለች ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ዎያኔዎቹ ፤ እንኳንስ ለኢትዮጵያ ፤ ነጻ እናወጣዋለን ብለው ለተነሱለት የትግራይም ሕዝብ ቢሆን ደንታ የላቸውም ።

ይኸንን መናገርና መቀበል የመረረ ቢሆንም ሀቁ ግን ይህ ነው። ሀቁን ተገንዝቦ ኀላፊነትን የመቀበል ተግባርና ግዴታ የሚወድቀው የአንድነት ኀይሎች በሚባሉት ትከሻ ላይ ነው። የአንድነት ኀይሎች፤ የየድርጅቶቻቸው የፖለቲካ ፕሮግራምም ይሁን ፤ ድርጅታዊ ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከላይ በተጠቀሰው ዐውደ ኃሳብ ላይ ግን እንዲስማሙ ይጠበቅባቸዋል ። **ይህንን አምኖ መቀበልና በተግባር መተርጎሙ ቅድመ-ግዴታ ሊሆን ይገባል።** በአሁኑ ጊዜ፤ የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም የማስጠበቁ ኀላፊነት የመሸከም ተልዕኮ ያረፈው፤ በአንድነት ኀይሎች እጅ መሆን እንዳለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በአንክሮ ይገነዘባል። ተግባራዊ እንዲሆንም ጓጉቶ ይጠብቃል ።

" ባተሌን ሲታገሱት የፈሩት ይመስለዋል " እንዲሉ፤ ዎያኔወች፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታጋሽነት፤ እንደ እንዝኅላልነት፤ ትዕግስቱን እንደ ቂልነት፤ አስተዋይነቱን እንደ አላዋቂነት ፤ አለመደራጀቱን እንደ ኋላ ቀርነት፤ የኃላፊነት ስሜቱንም እንደ ግድየለሽነት ፤ አርቆ ተመልካችነቱንም እንደ ፍርሀት አድርገው በመቁጠር እስከ አሁን ደረስ፤ መሳቂያና መቀለጃ ሲያደርጉት ቆይተዋል። ማፌዣና መተረቻ እያደርጉት ባጅተዋል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ አለማንቀሳቀስ ተገንዝበው ፤ ለራሳቸው መለበሚያና መደራጃ፤ መደላደያና መበልጸጊያ አድርገውታል። ስበዕናውን አዋርደው፤ ግርማ- ሞገሱን ጥላሸት ቀብተው፤ ሀገራዊ ዜግነቱን በጎሰኝነት ቁና ሰፍረው፤ ኢትዮጵያዊነት ልዕልናውን በጎጥ ሸለቆ ከልለው፤ ለመግዛት ዕቅድ አውጥተው፤ እነሆ የተመኙትን አግኝተዋል ።

የሀገር ቤቱን ተቃውሚዎች <u>" እንቅስቃሴ በቁጥጥር አውለነዋል</u> " በለው በመመኘት ፤ የውጩን ኀይል ( ዲያስፖራውን ) ለመተናኮል የልብ ልብ እስከማግኘት ደርሰው፤ የዓለም አቀፍን ህግ እስከ መጣስ ተዳፍረዋል። ድምበር- ዝለል ውንብድና በማካሄድ ስደተኞችን እያፈኑ እስከመውሰድ በቅተዋል ። የሀገሪቱን ፤ የፖለቲካ ምኅዳር፤ የኢኮኖሚ አውታሮችንና ማኅበረ ሰብዓዊና ሃይማኖታዊ መስተጋብሮችን በብቸኝነት ተቆጣጥረዋል። የፀጥታና የደኅንነት መዋቅሮችን በመዳፋቸው አስገብተዋል። በወታደራዊ መስፈርታቸውም ይመጻደቃሉ። ይህንን መስፈርት አውጥተው አውርደው፤ ሀገሪቱን በናዚ ጀርመን አምሳያ፤ ሁሉ-አቀፍ ኀይል ( ቶታሊታሪያን ) አገዛዝ ስር አድርገናታል ብለው ደምድመዋል ። ለዚህ ድምዳሜ ያበቃቸውም፤ ደግሞ የውጭ ጌቶቻቸው ርዳታና ትብብር ነው ።

አሁን ያላቸው አንጻራዊ ኀይል ግን ወደፊት ከሚነሳው የሕዝብ አመፅና ዕሳተ-ገሞራ አንጻር ሲገመገም፤ ማዕበሉን የሚቋቋምበት ደፍረትና ሀሞት አይኖራቸውም። ከሕዝባዊ ቁጣና አመፅ ሊያተርፋቸው የሚችል የመከላከያ ወረዳ አያገኙም። የከደቱ የኢትዮጵያ ሕዝብና ምደሪቱም ትከዳቸዋለች። የውጭ ባዕዳን ወዳጆቻቸውም ፤ጀንበሯ ሳተጠልቅ እንደሚከዷቸው ጥርጥር አይኖርም። በዚያ ቀውጢ ሰዓት፤ እንኳንስ ደሙን የሚልግሳቸው ቀርቶ፤ ደማቸውን የሚጠርጉብት ፋሻ የሚያቀብላቸው ወዳጅ አይገኙም። ወያኔዎቹ የተማመኑበት የነበልባልና የአጋዓዚ ጦርም፤ ማዕበል እንደገባበት ነዶ ይበታተናል። ሀገር-ወዳድ የሆኑ የጦር አዛዦችም፤ የኀይል ሚዛኑን በማየት፤ ወደ ሕዝብ ጎራ ሰልፋቸውን እንደሚያሳምሩ የታወቀ ነው። ደሙን እየገበረ ነፃንቱን ለማስከበር የተነሳሳው ሕዝብ የማንንም ርዳታና ትብብር አይጠብቅም። ያ ምፅዓት ከመድረሱ በፊት፤ የዎያኔ አገልጋዮች፤ ሀገሪቱን ከሚመጣው አደጋ ለመከላከል የበኩላቸውን የቤት ሥራ ለመስራት ጊዜው አሁን ነው ።

**" በመስታዊት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ድንጋይ ለመወርወር የመጀመሪያዎቹ ሊሆኑ ኣይገባም "** እንደሚባለው ፤ የመከላካያ ሠራዊት አባላት አፈ ሙዙን ወደ ማን ላይ ማዞር እንዳለባቸው ሊያውቁት ይገባል። ወገናቸው ለሆነው ሕዝብና ሀገራቸው ለሆነችው የኢትዮጵያ ምድር ታሪክ የሚሰሩበትን ቀን በክብር እንደሚጠባበቁ ሁሉም ዜጋ ጓጉቶ የጠብቃል።

የአንድነት ኀይሉ፤ ጥቃቅን ልዩነቶችን እያስወገደ፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የማስጠበቅ አጀንዳውን ካስቀደመ፤ ሀገሩን ከከፋፋዮች ለማድን የሚያድርገው ትግል ግቡን ይመታል። የኢትዮጵያን ሕዝብ እምባ ማደረቅ ቀድሚያ የሚሰጠው ቢሆንም፤ ዕምባው መድረቅ ካልቻለ ግን ዕምባው ወደ ደም እንደሚለወጥ ወያኔዎቹ ይስቱታል ተብሎ አይጠበቅም። ምክንያቱም የያዛቸው ዕኩይ ባኅርይና የጥፋት አባዜ ፤ መልካሙን እንዲያደርጉ ስለማይፈቅድላቸው ነው ። በመሆኑም ፤ ኢትዮጵያን የማዳኑ ተልዕኮ በአንድነት ኀይሉ ጫንቃ መሆኑን ተረድቶ ግዴታውን መወጣት አለበት ። ዕምባ ወደ ደም የሚለወጥበት ዓላማ ፤ ነፃነትን ለመጎናጸፍ ነው ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !